31ኛ ዓመት ቁጥር 206
አሶሳ፣
የካቲት/ 2017 ዓ.ም

ፖ.ሳ.ቁ. 293
ያንዱ ዋጋ------------

# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

## ልሣነ- ሕግ ጋዜጣ

## LISAN HIG-GAZETA

### Of the Council of the Benishangul Gumuze Regional State

**በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት**

**ጠባባቂነት የወጣ**

## አዋጅ ቁጥር 206//2017

## "የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዳኝነት አስተዳደር ጉባኤ ማሻሻያ አዋጅ"

### መግቢያ

በፍትህ አስተዳደር ውስጥ ከፍተኛና ወሳኝ የሆነውን ሚና የሚጫወቱት ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራቸውን ከማናቸውም ውስጣዊና ውጫዊ ተጽዕኖ ነጻ ሆነው በገለልተኛነትና በተጠያቂነት መንፈስ ማከናወን ያለባቸው በመሆኑ፤

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፍርድ ቤቶች ዳኞች ግልጽ፣ ገለልተኛና ተዓማኒ በሆነ አሰራር የሚሾሙበትን ሥርዓት በመዘርጋት የፍርድ ቤቶችንና እና የዳኞችን ብቃት፣ ነጻነት፣ገለልተኝነትና ተጠያቂነት በማረጋገጥ የዳኝነት ሥርዓቱ የሕግ የበላይነትን ያስከበረ እና የሕዝብ አመኔታን ያገኘ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የዳኝነት ሥርዓቱን ለማጠናከር የክልሉ ፍርድ ቤቶች በበጀት ምደባና አስተዳደር፣በሰው ሀብት ቅጥርና ምደባ እንዲሁም አስተዳደር ራሳቸውን ችለው የሚሰሩበትን የሕግ ማዕቀፍ እና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

እነዚህን መሰረታዊ ዓላማዎች ለማሳካት አሁን ያለውን የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 164/2011 መሰረታዊ በሆኑ መልኩ በማስተካከል በአዲስ አዋጅ መተካት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህገ- መንግስት አንቀጽ (49(1) እና 3 (1) በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ" የቤኒሻንጉለ ጉሙዝ ክልል የዳኝነት አስተዳደር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 206/2017 "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1 **"ሕገ መንግሥት"** ማለት የተሻሻለው ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሕገ መንግሥት ነው፤

2 **"ምክር ቤት"** ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ማለት ነው፡፡

3. **"ፍርድ ቤት"** ማለት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የተቋቋመ የጠቅላይ ፣ የከፍተኛ፣ የወረዳ ፍ/ቤት ማለት ነው፡፡

4. **"ጉባኤ"** ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የተቋቋመው የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ነው፡፡ "ጽ/ቤት" ማለት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤው ጽ/ቤት ነው፡፡

5 **"ፕሬዚዳንት"** ማለት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ነው፡፡

6 "የጽህፈት ቤት ሀላፊ" ማለት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤትን እንዲመራ በጉባኤው የተሾመ ሰው ነዉ፡፡

7. **"ዳኛ"** ማለት በህግ አግባብ፣ በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ተመርጦ በክልሉ ምክር ቤት የተሾመ የተፈጥሮ ሰዉ ነው፡፡

8 **"ደንብ"** ማለት በጉባኤው የጸደቀ የዳኞች ሥነ-ምግባር እና የዲሲፕሊን ሥነ-ሥርዓት ደንብ እና ሌሎች በዚህ አዋጅ መሰረት በጉባኤው የሚወጡ ደንቦችን ይጨምራል፡፡

9. **"ተለማማጅ ዳኛ"** ማለት በዳኞች የአስተዳደር ጉባኤ ተመርጦ በምክር ቤት እስኪሾም ድረስ በጉባኤ ወይምበፕረዚዳንቱ ተመድቦ የሚሠራ የሕግ ሙያተኛ ነው፡፡

10. **“ሌሎ ች የጉባኤ ተሿሚዎች"** ማለት የጉባኤ ጽህፈት ቤት ሃላፊ ፣ዳይሬክቶሬቶች፣ ሸርዓ

ዳኞችን፣ ተከላካይ ጠበቃ፣ሬጅስትራር እና ሌሎችንም በጉባኤዉ የሚሾሙና የሚመደቡትን ይጨምራል፡፡

11.**"ኮሚቴ"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 መሰረት በጉባኤው የተቋቋመ ኮሚቴ ማለት ነው፡፡

12.**"የኮሚቴ አባል"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14/2/ በጉባኤ የተቋቋመ ኮሚቴ አባል የሆነ ነዉ።

13. **“የዳኝነት ሥነ-ምግባር ጥሰት”** ማለት በዳኞች የሥነ-ምግባርና የዲስፕሊን ክስ ሥነ-ሥርዓት ደንብ የሥነ ምግባር ጥሰት መሆኑ የተመለከተ ማናቸውም ድርጊት ነው፡፡

14. **“ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታ ማነስ”** ማለት በዳኝነት ሥነ-ምግባርና የዲሲፕሊን ሥነ-ሥርዓት ደንብ የተመለከተ ድርጊት ሲሆን በዳኝነት ሥራ ላይ ሞያው ከሚጠይቀው የትምህርትና የልምድ ችሎታ በታች የሆነ የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ስህተት መፈጸምን

ይጨምራል፡፡

15 **“በዳኛ የሚከናወን መሰረታዊ የዳኝነት ሥራ”** ማለት የጉዳዩን ፍሬ ነገር መለየትና አግባብነት ካለው ሕግ ጋር ማዛመድ፣ ጭብጥ መለየት፣ ጉዳዮችን ማከራከር፣ አቤቱታ መስማት፣ ምስክር መስማት፣ ትዕዛዝ፣ ብይን፣ ውሳኔ መስጠትና ማሰማት ማለት ነው፡፡

16. **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ የሰውነት ያለዉ አካል ነዉ፡፡

## አንቀጽ 3.ዓላማ

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

1. በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፍርድ ቤቶች የሚሾሙ ዳኞች ግልጽ፣ገለልተኛና ተዓማኒ

   በሆነ አሰራር የሚሾሙበትን ሥርዓት በመዘርጋት ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በብቃት፣ በሙሉ ነጻነት፣ገለልተኝነትና ተጠያቂነት የሚያከናውኑበትን አሰራር ማረጋገጥ፤

2. የዳኝነት ሥርዓቱን ከማናቸውም ውስጣዊና ውጫዊ ተጽዕኖና ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆኖ

   እንዲሰራ ማስቻል፤

3. የዳኝነት ሥርዓቱ የሕግ የበላይነትን ያረጋገጠ፡ እንዲሁም የሕዝብ እርካታ እና አመኔታን ያገኘ እንዲሆን ማድረግ፤

**አንቀጽ4. የተፈጻሚነት ወሰን፣**

ይህ አዋጅ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፍርድ ቤቶች፣ በማንኛውም ደረጃ በሚሾሙ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፍርድ ቤቶች ዳኞች፣ የጉባኤ አባላት፣ በዳኛ ማዕረግ ለተሾመ፣ ሬጅስትራር እና ተከላካይ ጠበቃ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**ምዕራፍ ሁለት**

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፍርድ ቤቶች ዳኞች አስተደር ጉባኤ ስለማቋቋም**

**አንቀፅ 5**

1. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ከዚህ በኋላ "ጉባኤ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. ጉባኤው በጽህፈት ቤት ሀላፊ የሚመራ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ቋሚ ጽህፈት ቤት እና አስፈላጊ ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

**አንቀፅ 6 የጉባኤው አባላት**

1.ጉባኤው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

ሀ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ኘሬዚዳንት ---------------------------------------- ሰብሳቢ፣

ለ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ------------- ምክትል ሰብሳቢ፣

ሐ/ በም/ቤቱ አፈ ጉባኤ የሚወከሉ አራት የምክር ቤቱ አባላት ----------- አባል፣

መ/ የክልሉ ፍትህ ቢሮ ሃላፊ ------------------------------------------------ አባል፣

ሠ/ ከጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኞች የሚመረጥ አንድ ዳኛ ------------------------- አባል፣

ረ/ የክልሉ የፍትህ አካላት ማሰልጠኛ ተቋም ዋና ዳይሬክተር------------ አባል፣

ሰ/ ከሁሉም ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ፕሬዚደንቶች ----------------------------------አባል፣

ሸ/ የጠቅላይ ፍ/ቤት ሸሪያ ዋና ቃዲ-----------------------------------------አባል

ቀ/ በሁሉም ከፍተኛ ፍ/ቤቶች የሚመረጥ አንድ ዳኛ ------------ አባል፣

በ/ ከወረዳ ፍ/ቤቶች የሚመረጥ አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ዳኛ -- 2 /ሁለት/ አባል፣

ተ/ የክልሉ ጠበቆች ማህበር ተመርጦ የተወከለ አንድ ጠበቃ…………. አባል፣

ቸ/ የክልሉ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሃላፊ ……………………….አባል፣

2. ፕሬዚዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ሰብሳቢዉን ፕሬዚዳንቱን ተክቶ ይመራል፡፡

3. የጉባኤው አባላት የሥራ ዘመን ከክልሉ ም/ቤት አባላት የሥራ ዘመን ጋር አንድ ዓይነት ይሆናል፡፡

4. ማንኛዉም የጉባኤዉ አባል በጉባኤዉ የተወሰኑትን ደንቦች ወይም ዉሳኔዎች የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀፅ 7

## የሥራ ሚስጥር ስለመጠበቅ

1. ጉባኤዉ በይፋ እንዲገለጹ ያላደረጋቸዉ የጉባኤ ዉይይቶች ፣የቀረቡ ሀሳቦች እና የተደረጉ ክርክሮች ይዘት ሚስጥራዊነት የተጠበቀ ይሆናል፡፡

2. ማንኛዉም የጉባኤ አባል ወይም በጉባኤ ስብሰባዎች ላይ የሚሳተፉ ሰዉ ምስጥር የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

3. በንኡስ ቁጥር 1 እና 2 የተገላጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የጉባኤ አባላት ይህን ጥብቅ ዲሲፕሊን ያልተላበሰ መሆኑን የጉባኤ ሰብሳቢ በተረዳ ጊዜ ጉዳዩን ለአስ/ጉባኤ አቅርቦ ሀሳቡ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲደገፍ ከጉባኤ አባልነት እንዲሰረዝ ተደርጎ የወከለዉ አካል እንዲዉቅ እና በምትኩ ሌላ እንዲወከል ይደረጋል፡፡

## አንቀፅ 8 የጉባኤው ሥልጣንና ተግባር

1. ለክልል ፍርድ ቤቶች ዳኝነት ብቃት አላቸው ብሎ ያመነባቸውን ዕጩ ዳኞች መልምሎ ለሹመት ያቀርባል፤

2. የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የወረዳ ፍ/ቤቶች ፕሬዚዳንትነቶችን ጨምሮ ለክልሉ ዳኞች በዕጩነት የሚቀርቡትን ሰዎች መልምሎ እጩዎቹን በተመለከተ ከማንኛውም ሰው እና ቦታ ማስረጃዎችን ይሰበስባል ወይም እንዲሰበሰብ በማድረግ ብቁ የሆኑትን ለሹመት ክልል ምክር ቤት ያቀርባል።

3. በፕሬዚዳንቱ አቅራቢነት የፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ ሬጅስትራሮች፣ የረዳት ዳኛ እና ሌሎች የፍርድ ቤት የስራ ኃላፊዎችን ይሾማል፣ ደመወዛቸውን፣ አበላቸውን እና ሌሎች ጥቅሞቻቸውን እንዲሁም ከሥራ የሚሰናበቱበትን ሁኔታ ይወስናል።

4 በፌደራል ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 81/4/ መሠረት ከክልል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ

ለክልል ጠቅላይና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ዕጩ ዳኞች ዝርዝር መረጃ ለአስተያየቱን ለፌደራል የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ጽ/ቤት ይልካል፤

5 የጉባኤውን ጽ/ቤት አደረጃጀትና የሚሰራበትን መመሪያ ያወጣል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

6 ጉባኤው ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች የሚመሩበት የሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፤ ኮሚቴዎች የተመደቡባቸውን ኃላፊነት በብቃት መወጣታቸውን ይቆጣጠራል፤ በየወቅቱም ይገመግማል፤ በግምገማው መሠረት ውሳኔ ይሰጣል፤

7 በወረዳ እና ከፍተኛ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንቶች፣ እና ዳኞች ላይ የቀረበን የዲስፕሊን ኮሚቴ የሰጠዉን ዉሳኔ ሀሳብ ይመረምራል፤ይወስናል፡፡

8 የዳኞችን እድገት፣ ደመወዝ፣ አበል፣ እረፍት፣ ሕክምና እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ይወስናል፤

9.የክልል ፍ/ቤት ዳኞች እና ሌሎች የጉባኤ ተሿሚዎች የሚመሩበት የሥነ-ምግባር እና የዲሲፕሊን ክሶች የሚታዩበትን የሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል፤

10.የክልል ፍ/ቤቶች እጩ ዳኞች እና ሌሎች የጉባኤ ተሿሚዎች ምልመላ የሚከናወንበት ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፤

11.የክልል ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች፣ የስራ ሂደቶችንና ክልል ዳኞች የሥራ አፈፃፀም መመዘኛ ሥርዓት ያወጣል፣ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣ እንደ አስፈላጊነቱም በየጊዜው ያሻሽላል፡፡

12.ለጉባኤው አባላት የሚከፈለውን አበል ይወስናል፤

13.የክልል ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ሰራተኞች የሚተዳደሩበትን ደንብ ያወጣል።

**አንቀፅ 9 <u>የጉባኤው ሰብሳቢ ሥልጠንና ተግባር</u>**

የጉባኤው ሰብሳቢ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል

የጉባኤውን ስብሰባዎች በሰብሳቢነት መምራት፤

1. ከጽ/ቤት ኃላፊው ጋር በመመካከር አጀንዳ አዘጋጅቶ ለጉባኤው ማቅረብ፤
2. በጉባኤው የተመለመሉ እጩ የክልል ፍርድ ቤት ዳኞችን, የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ወረዳ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶች ለማሾም ዝርዝራቸውን ለክልል ምክር ቤት ማቅረብ፤
3. የጉባዔውን ጽሕፈት ቤት በበላይነት መምራት፣ መቆጣጠር፤

4. በጉባኤዉ ስር ለተቋቋሙት ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች የሚከፈለዉን አበል ይወሰናል፡፡

## አንቀፅ 10 የጉባኤው ምክትል ሰብሳቢ ሥልጣን ተግባር

የጉባኤዉ ምክትል ሰብሳቢ የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባር ይኖሩታል።

1. ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤
2. ሌሎች በሰብሳቢ ተለይተው የሚሰጡን ተግባራት ያከናዉናል፤

## አንቀፅ 11 የጉባኤው ስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

1. ጉባኤው በ3 ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማናቸውም ጊዜ ሊሰበስብ ይችላል፤
2. ከጉባኤው አባላት 2/3ኛ (ሁለት ሶስተኛ) የሚሆኑት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፤
3. በዚህ አዋጅ ጉባኤዉ በልዩ ሁኔታ ድምጽ እንዲሰጥባቸዉ የተደነገጉት እንደተጠበቀ ሆኖ ፤የጉባኤው አባላት በድምፅ ብልጫ ውሳኔዎችን ያሳልፋሉ፤ ሆኖም ድምጹ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፤
4. የዲሲፕሊን ክስ የቀረበበት ማንኛውም/ዋም የጉባኤ አባል ጉዳዩ ታይቶ እስከሚያልቅ ድረስ የቀረበበትን ዲስፕሊን በሚመለከት የሚደረግ የጉባኤው ጠቅላላ ስብሰባም ሆነ በተመደበበት ኮሚቴ ስብሰባ ላይ በአባልነት መቀመጥ አይችልም፤
5. በዚህ አንቀጽ ከዚህ በላይ ከንዑስ አንቀጽ 1-4 የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ጉባኤው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ማውጣት ይችላል፤

## አንቀፅ12. የጉባኤው አባላትን ሥልጣን እና ኃላፊነት በውክልና መስጠት የማይቻል ስለመሆኑ

ማንኛዉም የጉባኤዉ አባል በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን እና ተግባር በውክልና ለማናቸውም ተቋም ወይም ግለሰብ መስጠት አይችልም፡፡

## አንቀፅ 13 ቃለ መሀላ

1. የጉባኤው አባሎች የተጣለባቸውን ከፍተኛ ሀላፊነት ባላቸው ዕውቀትና ልምድ በነጻነት፣ በገለልተኝነት፣ እና በዚህ አዋጅና በአገሪቱ ሕጎች መሰረት በአግባቡ የሚፈጽሙ ለመሆናቸው ሥራ ከመጀመራቸው በፊት በጉባኤው ሰብሳቢ አማካኝነት በቃለ መሀላ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
2. በክልል ምክር ቤት ጉባዔ ፊት ቃለ መሀላ ከገቡት ውጭ ላሉ የጉባዔ አባላት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

3. የሚምሉትም እኔ ------------------------ በዛሬው ዕለት -------- የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አባል ሆኜ እንድሰራ ስመረጥ የተጣለብኝን ከፍተኛ ኃላፊነት በታማኝነትና በትጋት ልፈጽም ቃል እገባለሁ በማለት ነዉ ፡፡

## አንቀፅ 14 የጉባኤው ኮሚቴዎች

1. ጉባኤው ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት እንዲያስችለው የጉባኤውን አባላት የያዙ ኮሚቴዎችን ሊያዋቅር ይችላል። ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ የጉባኤዉ አባል ያልሆኑ ሰዎችን የያዙ ኮሚቴዎችን ሊያዋቅር ይችላል።
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባኤው የሚከተሉትን ኮሚቴዎች ያደራጃል፤

ሀ) የዕጩ ዳኞች ምልመላ፣ ፈተና፣ የዳኞች ዕድገት እና ዝውውር ጉዳዮች ኮሚቴ፤

ለ) የሰው ሀብት፣ የበጀት፣ የፋይናንስ፣ የደመወዝ፣ አበልና ጥቅማ ጥቅም ጉዳዮች ኮሚቴ፤

ሐ) የዳኞችሥነ-ምግባርና የዲስፕሊን ኮሚቴ፤

3. የጠቅላይ ፍ/ቤት አጣሪ ባለሙያዎች በተለያየ ምክንያት ተደራሽ መሆን ባልቻሉበት ዞንና ወረዳ በቅርበት ለሚገኘዉ ወረዳ ወይም ዞን ላይ ለሚሰሩ ዳኞች ዉክልና በመስጠት ማጣራት ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ በዳኝነት ሥነ-ምግባር እና የዲሲፕሊን ሥነ-ሥርዓት ደንብ ይወሰናል፡፡
4. የጉባኤው ኮሚቴዎች ለእያንዳንዳቸው ቋሚ ባለሙያዎች ከጽ/ቤቱ ይመደብላቸዋል፡፡ ባለሙያዎቹም የኮሚቴዎቹን የቀን ተቀን ሥራ ከኮሚቴዎቹ ሰብሳቢዎች እና ከጽህፈት ቤቱ ኃላፊ በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት ይሰራሉ፤
5. የኮሚቴው አባላት የተመደቡበትን ኃላፊነት በማናቸውም መልክ ለሌላ የጉባኤው አባል ወይም ለሌላ ወገን በውክልና ሊሰጡ አይችሉም፡፡
6. ኮሚቴዎቹ ጉባኤው በሚያወጣው የአሰራር ደንብ መሰረት ሥራቸውን ያከናውናሉ፡፡

## አንቀፅ 15 ስለጉባኤው ጽ/ቤት

1.የጉባኤው ጽ/ቤት አንድ የጽ/ቤት ኃላፊ፣ በጀት እና አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

2 የጽ/ቤቱ ኃላፊ ጉባኤው በሚያወጣው መስፈርት መሰረት በጉባኤው ይሾማል፤

3. የጽ/ቤት ኃላፊ ተጠሪነቱ ለጉባኤው ሰብሳቢ ይሆናል፤

4 የጽ/ቤት ኃላፊ የጉባኤው ስብሰባዎች ፀሐፊ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 16 የጉባኤው ጽ/ቤት ተግባር እና ኃላፊነት

የጉባዔው ጽሕፈት ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተግባራት እና ሀላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. የጉባኤውን ዓመታዊ የሥራ እቅድና በጀት ማዘጋጀት፤ሲፈቀድም በጀቱን ማስተዳደር፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33 መሰረት በክልል ዳኞች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በመቀበል ለሚመለከተው ኮሚቴ መምራት፤በአቤቱታዎቹ ላይ ኮሚቴው ያቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤው ማቅረብ፤
3. በጉባኤው የተወሰኑ ውሳኔዎች በሰብሳቢዉ ፊርማ ለሚመለከተዉ አካል እንዲደርስ ማድረግ፤ ዉሳኔዎቹ መፈጸማቸዉን መከታተል፤
4. የክልል ዳኞች የግል ማህደርን ማደራጀት፣ አስፈላጊ መረጃዎችም በማህደሮቹ መግባታቸውን መከታተል፣ የግል ማህደሮች በሚመለከተው ኮሚቴ ሲፈለጉ ማቅረብ፤
5. የጉባኤውን እና የኮሚቴዎችን የስብሰባ ቃለ ጉባኤዎችን ሌሎች ሰነዶችን በአግባቡ አደራጅቶ መያዝ፤
6 በጉባኤው በሚቋቋሙ ኮሚቴዎች ውስጥ በቋሚነት የሚያገለግሉ ከኮሚቴው ኃላፊነት ጋር ተዛማጅ እውቀት እና ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች በቋሚነት መመደብ፤ሥራቸውንም መከታተል፤
7. የዳኞች የሥራ አፈጻጸም ምዘና ጉባኤው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በፍርድ ቤቱ አስተዳደር በቋሚነት መከናወኑን ማረጋገጥ፤
8. የክልል ዳኞችን አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ከሚመለከታቸው ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች እና ባለሙያዎች ጋር በመሆን አፈፃፀማቸውን መከታተል፤

## አንቀፅ 17፣ የጉባኤው ጽ/ቤት ኃላፊ ሥልጣን እና ተግባር፣

የጉባኤው ጽ/ቤት ኃላፊ የሚከተሉትን ስልጣን እና ተግባር ይኖሩታል፡

1. ከጉባኤው ሰብሳቢ በሚሰጥ አቅጣጫ መሰረት የጉባኤውን የስብሰባ አጀንዳዎች ከጉባኤው ሰብሳቢ ጋር በመሆን ማዘጋጀት፤ ከስብሰባው ቀን ቢያንስ ሶስት ቀናት አስቀድሞ ለጉባኤው አባላት እንዲደርስ ማድረግ፤

2 በጉባኤው ስብሰባዎች ላይ በፀሐፊነት መገኘት፤ ቃለ ጉባኤ መያዝ፤ ቃለጉባኤዎቹ በአባላቱ መፈረማቸውን ማረጋገጥ፤

3. የጉባኤውን ጽ/ቤት የቀን ተቀን ሥራ በኃላፊነት መምራት፣መቆጣጠር

4. የጉባኤውን የተለያዩ ኮሚቴዎች ቢሮ ማደራጀት፤ የኮሚቴዎቹን ባለሙያዎች እና ረዳት ሠራተኞችን መመደብ፤

5. የጉባኤው አባላትን አበል በየጊዜው መክፈል፤

6. በጉባኤ ስር ለተቋቋሙት ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ዉሎ አበል ይወስናል ያስፈጽማል፡፡

4. ከኮሚቴ ሰብሳቢዎች ጋር በመመካከር የጉባዔውን ስትራቴጃዊ እና ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት በማዘጋጀት ለጉባዔው ሰብሳቢ ማቅረብ፣

8. የጽህፈት ቤቱን ሠራተኞች ማስተዳደር፤ መቆጣጠር፤

9. ስለጉባዔው ዕቅድ አፈጻጸም በጉባዔው በተጠየቀ ጊዜ በጉባኤው ሰብሳቢ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ሪፖርት ማቅረብ፤

10. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 የተዘረዘሩትን ተግባራት በሙሉ መፈጸም፣ማስፈጸም በጉባኤው ሰብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ማከናወን፤

11. የክልሉ ዳኞች በሌሎች ሕግ አግባብ በጡረታም ሆነ በጤና እክል ምክንያት ከዳኝነት ሙያ ለሚሰናበቱ በህግ የተፈቀደላቸውን መብትና ጥቅሞች ዕቅድ መያዝና ተገቢውን ክፍያ እንዲያገኙ ማድረግ፣

## አንቀፅ 18 ስለጉባኤው አባላት የሥራ ዘመን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 (1) ሀ፣ ለ፣ ሠ እና ሰ፣ ሸ ከተመለከቱት በስተቀር የሌሎች የጉባኤው አባላት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም የሥራ ጊዜዉን የጨረሰ የጉባኤ አባል ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን ብቻ ድጋሚ ሊመረጥ ይችላል፡፡

## አንቀፅ 19 የጉባኤው አባሎች ሥራቸውን ስለሚለቁበት ሁኔታ

1 በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 (1) በፊደል ሀ፣ ለ፣ ሠ ፣ ሰ፣ ሥ፣ ሸ እና በ ከተመለከቱት በስተቀር ማንኛዋም የጉባኤ አባል፤

ሀ. ከደንብ መተላለፍ ውጭ በሆነ ወንጀል ተከሶ ሲፈረድበት፣

ለ. በጤና ችግር ምክንያት ስራውን በአግባቡ ማከናወን ሲሳነዉ፤

ሐ. ይህን አዋጅ ወይም የጉባኤውን የውስጥ የአሰራር ሥነ ሥርዓት ባለማክበሩ፣ የጉባዔውን ሚስጥር ያልጠበቀና የስነምግባር ግደፈት የፈፀመ ሲሆን ጉዳዩ ለጉባኤው ቀርቦ ለአባልነት ተገቢ አለመሆኑ ከጉባኤው ጠቅላላ አባላት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲወሰን፤

መ. በሌላ ማናቸውም ምክንያት በጉባኤው ላለዉ ከፍተኛ ሀላፊነት አባል ሆኖ ለመቀጠል የማይችል ሲሆን እና በጉባኤዉ ሲወሰን፤ ከጉባኤው አባልነት ይሰናበታል፡፡

ሠ. ማንኛዉም/ዋም የጉባኤው አባል ከጉባኤው አባልነት በፈቃዱ ለመልቀቅ ቢፈልግ በጽህፈት ቤቱ በኩል ከአንድ ወር አስቀድሞ ለጉባኤው በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

### አንቀፅ 20 የዳኞች ሹመት፣ ሥልጠና፣ የሥራ ዘመንና ከኃላፊነት መነሳት

### የክልል ፍርድ ቤቶች ዳኛ ሆኖ ለመሾም የሚያበቁ አጠቃላይ ሁኔታዎች፤

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21፤22 እና 23 የተደነገጉት ተጨማሪ ሁኔታዎች በቅደም ተከተል ለክልል ወረዳ ፍርድ ቤት፤ ለዞንና ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለሚሾሙ ዳኞ ያላቸው ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉተን ሁኔታዎች የሚያሟላ በክልል ፍርድ ቤቶች ዳኛ ሆኖ ሊሾም ይችላል፤

1. በዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆነ/ች፤
2. ከፍተኛ ግብረገብነት (ሞራል) ያለዉ/ላት፣ ጨዋነቱ/ቷ፣ ቅንነቱ/ቷ፣ ሀቀኝነቱ/ቷ የተረጋገጠ፤ እና ሕዝብ ከሚነቅፋቸው ሞራል ነክ ልማዶች፣ ሱሶችና አስነዋሪ ልማዶች የራቀ፤
3. በታማኝነቱ፣ በሥራ ወዳድነቱ/ቷ፣ በእውቀትና በጤንነት የተሟላ ሆኖ የዳኝነትን ከፍተኛ ኃላፊነት ለመሸከም ባለዉ/ላት ችሎታና ፈቃደኝነት ለቦታው ተገቢ የሆነ፤
4. የህግ ሙያ ተነሳሽነት እና ለሕግ የበላይነት መከበር ቁርጠኛ የሆነ፤
5. ዳኛ ሆኖ ለመስራት ሙሉ ፍቃደኛ የሆነ፤
6. ከደንብ መተላለፍ ውጭ በወንጀል ተከሶ ያልተቀጣ፤
7. ዕድሜዉ ከ 25 ዓመት ያላነሰ፤
8. እውቅና ካለው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በሕግ ትምህርት የተመረቀ እና በዳኞች መተዳደሪያ ደንብ በሚወጣው መመዘኛ መስፈርትን የሚያሟላ፤
9. በየደረጃዉ ላሉ ፍ/ቤቶች ዳኞች እና ሌሎች የጉባኤ ተሿሚዎች የተፈላገ የትምህርት እና የስራ ልምድ የመመዘኛ መስፈርት እና ሌሎች ጉዳዮች በመተዳደሪያ ደንብ ዝርዝሩ ይወሰናል፡፡

### አንቀጽ 21 የዳኞች የሥራ ዘመን

1 በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27 ዳኞች ከሥራ ስለሚሰናበቱት ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛዉም የክልል ዳኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜ 60 ዓመት ይሆናል፡፡ 55 ዓመት እድሜ የሞላ ዳኛ ከፈለገ ጡረታ ሊወጣ ይችላል።

2 በዚህ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 1 የተጠቀሰዉ እንደተበቀ ሆኖ 25 አመት በመንግስት ስራ

ያገለገለ የክልል ዳኛ በ55 አመቱ ሲፈልግ ጡረታ ሊወጣ ይችላል።

1. ከአቅም በላይ በሆነ አሳማኝ ችግር ወይም የዳኝነት ስራ ለመስራት የማያስችል ህመም ምክንያት የዳኝነት ስራዉን ማከናዎን ያልቻለ እንደሆነ ቢያንስ 20 /ሀያ/ አመት በክልሉ ባለ ፍርድ ቤት በዳኝነት ያገለገለ ዳኛ ጡረታ እንዲወጣ ጉባኤዉ ሊወስን ይችላል።
2. በዚህ ህግ ያልተሸፈኑ ከጡረታ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ አግባብነት ያላቸዉ የመንግስት ሰራተኞች የሚመለከቱ የጡረታ ህጎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

## አንቀፅ 22 የዳኞች የደረጃ ዕድገት እና ዝውውር

1 አንድ የክልል ፍርድ ቤት ዳኛ ተሹሞ ባለበት ፍርድ ቤት የደረጃ ዕድገት የሚያገኘዉ በሥራዉ ላይ ባሳየዉ ግልጽ ብቃት፣ትጋት፣አገልግሎት እና መልካም ሥነ-ምግባር ላይ ብቻ ተመስርቶ በሚቀርብ ምክረ ሀሳብ መሰረት በጉባኤው ሲወሰን ነው፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

2 ጉባኤዉ አስፈላጊ ሲሆንና በቂ ምክንያት ሲኖር ዳኛ ከአንድ የክልል ፍርድ ቤት ደረጃ ወደ ሌላ የፍርድ ቤት ደረጃ በጊዜያዊነት መድቦ ሊያሰራ ይችላል፡፡

3 ዳኛ ከችሎት ወደ ችሎት ወይም ከምድብ ችሎት ወደ ምድብ ችሎት ለማዘዋወር ልዩ ሞያዊ ክህሎትን፣ብቃትን፣ልምድን እና የዝውውሩን አስፈላጊነት መሰረት በማድረግ ከክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ጋር በመመካከር በየደረጃው ባሉ የክልል ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች አማካኝነት ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 23 የዳኞች ሥልጠና

ዳኞች ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ብቃታቸውን ለማሳደግ በሚዘጋጀው ስልጠና የመሳተፍ ግዴታ አለባቸው፡፡

## አንቀፅ 24 ስለዳኞች ደመወዝ

1 የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንትና ሌሎችየጉባኤ ተሿሚዎች እና የክልል ዳኞች ደመወዝ የዳኝነት ሥራን ክብር ለመጠበቅ፣ ሀላፊነትን በአግባቡ ለመወጣት እንዲያስችል እና ኑሮአቸውን በአግባቡ ለመምራት በቂ ነው ተብሎ የሚገመት ክፍያን መነሻ በማድረግ በጉባኤው ይወሰናል፡፡

2 የዳኞች ደመወዝ ሌሎች ጉባኤ ተሿሚዎች የኑሮ ሁኔታን መሰረት በማድረግ በየጊዜው ሊሻሻል ይችላል

## 25 የዳኞችና ሌሎች ጉባኤ ተሿሚዎች ጥቅማ ጥቅሞች

1. አግባብነት ያላቸዉ የዳኞችን መብቶች እና ጥቅሞች የሚደነግጉ ህጎች እንደተጠበቁ ሆነዉ በስራ ላይ ያለ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት የቪ.አይ. ፒ አገልግሎት ያገኛሉ፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ የዳኞች ጥቅማጥቅም ዝርዝር ጉዳይ በሚመለከት ጉባኤው ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## አንቀፅ 26 የዳኞች ዕረፍት

1 ዳኞች የወሊድ፣ አባትነት፣ የእክል እና ሌሎች እረፍቶች ይኖሯቸዋል፡፡ ዝርዝሩ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በሚያወጣዉ ደንብ ይወሰናል፡፡

## አንቀፅ 27 የዳኞች የሥራ ስንብት

1 ማንኛዉም የክልል ፍርድ ቤት ዳኛ በሚከተሉት ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር ከዳኝነት ሥራዉ አይነሳም፡፡

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 በተመለከተው የጡረታ መውጫ እድሜ ሲደርስ ወይም ዳኛዉ 60 አመት ሞልቶት በጡረታ መሰናበት ሲፈልግ ወይም 25 አመት አገልግሎ በ55 ዓመት መሰናበት ሲፈልግ

ለ. ከዳኝነት ሥራ ለመልቀቅ ጥያቄ ሲያቀርብ የሁለት ወር ቅድሚያ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፤

ሐ. ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታ ማነስ ሲታይ እና ይህም በጉባኤው ተረጋግጦ ከዳኝነት ሥራ እንዲሰናበት ሲወሰን፤

መ. የዳኝነት ስራዉን በአግባቡ ለማከናወን የማያስችል ህመም ሲያጋጥመዉ

ሠ. የሥነ-ምግባር ጥፋት ፈጽሞ ሲገኝ እና ይህም በጉባኤው ሲረጋገጥ እና ከዳኝነት ሥራ እንዲሰናበት ሲወሰን፤

2.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) እና (ሠ) በተመለከቱት ሁኔታዎች ዳኛ ከሥራ እንዲሰናበት ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ ተፈጻሚ የሚሆነው ለክልል ምክር ቤት ቀርቦ ሲፀድቅ ነዉ፡፡

## አንቀፅ 28 ከስራ ስለተሰናበተ ዳኛ ክልከላዎች

1. ስለጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥ የሚደነግጉ ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው ከሥራዉ የተሰናበተ የክልል ዳኛ አስቀድሞ ይሰራበት በነበረው የክልል ፍርድ ቤት ደረጃ በሚገኝ ማናቸውም ችሎት በሰራበት መዝገብ ጉዳይ በጠበቃነት ተከራካሪዎችን

ወክሎ መቅረብ አይችልም፡፡

2. በዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት ከሥራው የተሰናበተ የክልል ዳኛ ከሥራ ስንብት ጋር በተያያዘ ለክልል ዳኞች በሕገ የተፈቀዱ ከጡረታ ዉጭ ያሉ ጥቅማጥቅሞችን አያገኝም፡፡

## ምዕራፍ አራት
## የዳኞች መብት
### አንቀፅ 29. የመናገር እና የመፃፍ ነፃነት

የዳኝነትን ነጻነት እና ገለልተኝነት መርሆችን እና በዳኞች የዲስፕሊን ደንብ የሚቃረን እስካልሆነ ድረስ ዳኞች በሕገ መንግሥቱ እና ሌሎች የሕግ ድንጋጌዎች በተረጋገጠው መሠረት የመናገር፣ የመፃፍ፣ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ተሳትፎ የማድረግ፣ መብት አላቸው፡፡

### አንቀፅ 30. የፖለቲካ ፓርቲ አባል ስላለመሆን እና ፓለቲካዊ ተሳትፎ

1. በየትኛውም ደረጃ ባለ የክልል ፍርድ ቤት የተሾመ ዳኛ የማናቸውም የፖለቲካ ድርጅት አባል መሆን፣ ወይም የፖለቲካ እንቅስቃሴ አራማጅ ወይም ደጋፊ ወይም በፖለቲካ ፓርቲ ስብሰባዎች ላይ ተሳታፊ መሆን አይችልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዳኞች የመምረጥ መብት አላቸው፡፡ማንኛውም የክልል ዳኛ የፖለቲካ ፓርቲን ወክሎ ወይም በግል በምርጫ ለመወዳደር የፈለገ እንደሆነ ምርጫው ከሚካሄድበት ቀን አንድ ዓመት ቀድሞ የዳኝነት ሥራውን መልቀቅ አለበት፡፡

## ምዕራፍ አምስት
## ስለዳኝነት ነጻነት፣ ግልጽነት፣ ገለልተኝነት እና ተጠያቂነት
### አንቀፅ 31 የዳኝነት ሥራን በግልጽ፣ በገለልተኝነት እና በተጠያቂነት መንፈስ ስለማከናወን

1. በፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ማናቸውም ፍርድ፣ ብይን፣ ውሳኔዎች እና ትዕዛዞች ከማንኛውም የውስጥም ሆነ የውጭ ተጽዕኖ ነጻ ሆነው በሕግና ፍሬነገር ላይ ብቻ የተመሰረቱ መሆን አለባቸው፡፡
2. የክልል ፍርድ ቤቶች የሚያከናውኗቸው የዳኝነት ሥራ ተግባራት ለሕዝብ ግልጽ መሆን አለባቸው፡፡
3. በችሎት የሚደረጉ የዳኝነት ክንውኖች ለተከራካሪ ወገኖች፣ለሕዝብ እና ለመገናኛ ብዙሀን ክፍት ሆነው ለማስተናገድ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ዝርዝሩ የክልል

ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

4. ፍርድ ቤቶች ማናቸውንም ተከራካሪ ወገኖች ያለ አድልኦ በዕኩልነት የማስተናገድና በተለይ በወንጀል ተከሰው በጥበቃ ሥር ሆነው ጉዳያቸው በመታየት ላይ ያሉ ሰዎችን አያያዝ ሁኔታ የመከታተል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## አንቀፅ 32 ስለ ዳኛ ኃላፊነት

1 ማንኛውም የክልል ፍርድ ቤት ዳኛ በያዘውጉዳይ ላይ ግልጽ፣ ነጻና ገለልተኛ ሆኖ የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

2 በተለየ ሁኔታ በሕግ ካልተወሰነ በስተቀር ማንኛውም የክልል ዳኛ የዳኝነት ጉዳዮችን በግልጽ ችሎት የማየት ግዴታ አለበት፡፡

3 በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የክልል ዳኛ በዳኝነት ሥራው ላይ ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ ወይም በሕግ አግባብ መፈጸም ያለበትን ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ በዳኝነት ሥነ-ምግባር ጥሰት ተጠያቂ ይሆናል፤

4 አግባብነት ባለዉ ህግ ካልተወሰነ ወይም ጉባኤዉ ካልወሰነ በስተቀር ማንኛውም የክልል ፍርድ ቤት ዳኛ በዳኝነት ሥራው ላይ እያለ በሕግ አውጭው ወይም በአስፈጻው አካል ሥራ በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት ተመድቦ ሊሰራ አይችልም፡፡

## አንቀፅ 33. በሥነ-ምግባር ጥሰት ክስ ስለማቅረብ

1. በዳኝነት ሥራ አካሄድ ላይ ግልጽ የሆነ የዳኝነት ሥነ-ምግባር ጥሰት ተፈጽሟል ብሎ ያመነ ማንኛውም ሰው ወይም ስለ መፈጸሙ ማስረጃ ያለው ለዳኝነት አስተዳደር ጉባኤ ሰብሳቢ አቤቱታ፣ ወይም ጥቆማ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በተፈመ የዳኝነት ሥነ-ምግባር ጥሰት ምክንያት በዳኛው ላይ የዲስፐሊን ክስ የቀረበ እንደሆነ ክሱ በፍጥነት መታየትና መወሰን ያለበት ሆኖ ዳኛው የሚቀርብበትን ክስ የማወቅና የመከላከል መብት አለው: ዝርዝሩ በዳኞች ሥነ-ምግባር እና የዲሲፕሊን ሥነ-ሥርዓት ደንብ ይወሰናል፡፡
3. በዳኛ ላይ የዳኝነት ሥነ-ምግባር ጥሰት አቤቱታ ያቀረበ ሰው በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ከጉባኤ ጽ/ቤት የማወቅ መብት አለው፤
4. በሥነ-ምግባር ጥሰት ምክንያት በቀረበ ክስ በዳኛ ላይ የሚወሰድ የዲሲፕሊን እርምጃ በሕገመንግስቱ፣ በዚህ አዋጅና በሥነምግባር ደንቡ መሰረት ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡

5. ከዳኝነት ሙያ በዲስፕሊን ከተከሰሰ ዳኛ ከሥራ ማገድ የሚቻል ቢሆንም ደመወዝ ክፍያ ግን አይታገድም፡፡

<u>ምዕራፍ ስድስት</u>

**አንቀጽ 34. <u>የሰው ሀብት</u>**

1. ጉባኤዉ የክልሉን መንግስት ሰራተኞች ህግ ተከትሎ የራሱን ባለሙያ ሰራተኞች የመመልመል፣ የመቅጠርና የማስተዳደር ነፃነት አለዉ፡፡

**አንቀፅ 35. ቃለ መሐላ**

በማናቸውም ደረጃ የሚሾም የክልል ፍርድ ቤት ዳኛ ሥራዉን ከመጀመሩ በፊት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ መንግስቱ መሰረት ቃለ መሐላ ይፈጽማል፡፡ የቃለ መሃላዉም ይዘት የሚከተለዉ ይሆናል።

«እኔ ____________የክልል_______ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኘ ስሾም አንዱን ከሌላዉ ሳላበላልጥ፣ ከማንኛዉም ወገንተኝነት ነጻ ሆኜ የአገሪቱን ህገ-መንግስት፣ የክልሉን ሕገ መንግስት እና ሌሎች ህጎችን መሰረት በማድረግ ፍትህን ለማስፈን እና የህግ የበላይነትን ለማስከበር በፍጹም ነጻነት፣ገለልተኝነት እና ከፍተኛ ትጋት ተገልጋዩን ህዝብ ለመዳኘት ቃል እገባለሁ።

**አንቀፅ 36 ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

1. የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ደንቦችን ያወጣል፡፡
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህን አዋጅ እና ደንቦችን ለማስፈጸም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**አንቀፅ 37 የተሻሩ ሕጎች**

1. የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 164/2011 በዚህ አዋጅ ተሽሯዋል፡፡
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሌላ ሕግ፤ ደንብ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተመለከተ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**አንቀፅ 38 የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ይህ አዋጅ ከመጽደቁ በፊት ተጀምረው የነበሩ በዳኞች ላይ የቀረቡ የዲሲፕሊን ክሶች

በዚህ አዋጅ በተቋቋመው ጉባኤ ታይተው ይወሰናሉ፡፡

**አንቀፅ 39 <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በክልል ምክር ቤት ከጸደቀበት የካቲት 11 ቀን 2017 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አሶሳ**

የካቲት 11 ቀን 2017 ዓ.ም

**አሻድሊ ሐሰን አልአጀብ**

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ፕሬዚዳንት**